# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 33 ኛ ሳምንት
## ለሌሎች መልካም አርኣያ መሆን

**ዓላማ**
- ለሌሎች መልካም አርኣያ የመሆን ኃላፊነትን መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**
- ***" እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ።"*** ዮሐ 15÷13

**መግቢያ**
- ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዴት መኖር እንዳለብን አስተምሮናል፣በመልካም ሥራዎቹም ምን ማድረግ እንዳለብን ምሳሌ ሰጥቶናል።
- ዛሬም በቃልና በተግባር ማስተማሩን እናያለን።

**ትምህርቱ**
1. ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***" ጠላቶቻችሁን ወደዱ የሚረግሟችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ፤"*** ማቴ 5 ÷ 44 - 45 ሲል አስተምሮዋል።ለሚሰድቡትና ለሠቀሉት ምህረትን በመለመንም ተግባራዊ ምሳሌውን ትቶልናል። የክርስቶስ ሰቃዮች ከሥር ሆነው እየተሳደቡ እርሱ በመስቀል ላይ ሆኖ ***" አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ"*** ሉቃ 23÷34
2. ጌታችን ራሱን ለሌሎች አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር የለም ብሎ ነበር።(ዮሐ 15÷13) ራሱን በመስቀል በመስጠትም ምሳሌውን ትቶልናል።
3. ***"ሰው ከውኃ እና ከመንፈስ ዳግመኛ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግስት አይገባም።"*** ዮሐ 3÷5 ብሎ እንዳስተማረ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ አርኣያ ሆኖናል።
4. በመጨረሻም ከመሰቀሉ በፊት የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቧል። እንዲህም ብሎዋቸዋል። ***" እንግዲህ እኔ ጌታ እና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።"*** ዮሐ 13÷14-15

- ቅዱሳን ሐዋርያት ክርስቶስ እንዳዘዛቸው ፈጽመዋል። በፍቅር ወንጌልን ሰብከዋል፣ ለሌሎች አርኣያ ሆነዋል ሌሎቹም በህይወታቸው አርአያ እንዲሆኑ አስተምረዋል።
- የሚከተለው ለዚህ አብነት የሚሆነን የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ነው። ***" በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽህናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን።"*** 1ኛ ጢሞ 4÷12

**የዚህ ትምህርት ጠቃሚ መልዕክቶች**
- በህይወታችን ለሌሎች መልካም አርኣያ መሆን ያስፈልገናል።ወጣት ወንድሞች፣ እህቶችና ልጆች ከታላላቆቻቸው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም መማር አለባቸው። ክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነንም እኛም ስለሌሎች ምሳሌ መሆን አለብን።

**ማጠቃለያ**
- ክርስቶስ የተወልን ምሳሌዎች ፍቅር፣ ትኅትናና ሌሎች መልካም ስነ ምግባሮች ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዛሙሩ ጢሞቲዎስ እንደጻፈለት፤ እኛም ለሌሎች አርአያ መሆን ያለብን፡-

1. **በቃላቶቻችንና በንግግራችን**፡-ከሌሎች ጋር በመልካም ቃል ተናገራቸው ስትነጋገርም አስቀያሚና ክፉ ቃላትን ሳትጠቀም ይሁን።
2. **በልግስና** የቸገረውን እርዱ፣ለሌሎች ይሄንኑ አስተምሩ።
3. **በመንፈሳዊነት** የመንፈስ ፍሬ የሆኑትን ፍቅርን፣ሰላምን፣ትዕግስትን፣መልካምነትን …ወዘተ ፈጽሙ።
4. **በእምነት** በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላችሁን እምነት ጠብቁ እንደትዕዛዙም ኑሩ። በቤተክርስቲያን ሥርዓት አምልኮ መሳተፍ አለብን።የጸሎትና ጾም ሕይወትም የመንፈሳዊነት መገለጫና የእምነት ተግባራት ናቸውና እነዚህን አዳብሩ።
5. **ንጽህና** በሥጋና በነፍስ ንፁኃን ሁኑ። በስጋ ንፁሕ መሆን ማለትም አካላዊ ዝግጅቶችን ለምሳሌ መታጠብ፣ በሥርዓት መልበስ ወዘተ … ፈጽማችሁ ወደ ቤተክርስቲያን ለአምልኮ እንደምትመጡት ሁሉ ከጋብቻ በፊት ተገቢ ካልሆነ ግንኙነት ተጠበቁ።መንፈሳዊ ዝግጅቶች ማለትም መጸለይና ለምድራዊ እና ግብረገብነት የጎደላቸውን ነገሮች ከማድረግ ይልቅ መንፈሳዊ ነገሮችን ለማሰብና ለመለማመድ መዘጋጀት ነው።

**ጥያቄና መልመጃዎች**
1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አርአያ እንደሆነ ምሳሌ ጥቀሱ።
2. ቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዛሙሩን ጢሞቲዎስን ምን መከረው?
3. በተግባርና በቃል ማስተማር ለምን ይጠቅማል?
4. ሌሎች በተግባር ያስተማሩአችሁን መልካም ነገር አብራሩ።
5. ታናናሾቻችሁ የምትሰሩትን ይከተላሉ? እንዴት?

**ይቆየን።**